
## የሴቶች የግብረስጋ ብልት መግረዝ በስዊዘርላንድ ዉስጥ በህግ የተከለከለ ነው

በስዊዘርላንድ ዉስጥ የሴቶች የግብረስጋ ብልትን መግረዝ እንደ ኣካል ላይ ጉዳት ማድረስ ተቆጥሮ ነው የሚታሰበው። በዚህም ምክንያት የተከለከለ ነው። የዚህ ዓይነት ተግባር የሚፈጽም ሰዉም እስከ 10 ዓመት ድረስ በእስራት ሊቀጣ ይችላል። ግርዛቱ የሚደርስባት ልጃገረድ በፈቃደኝነት የተገረዘች የሆነ እንደሆነ እንኳን፣ ገራዡን ከመቀጣት ኣያድነዉም። የሴቶች የግብረስጋ ብልትን የገረዘ፣ በዚሁ ተግባር ወይም በዝግጅቱ የተሳተፈ ይቀጣል። ይህ ቅጣት ሁሉንም ተካፋዮችን ይመለከታል፥ ሓኪሙን፣ሓኪሟን፣ ገራዡን፣ ገራዧን፣ ወላጆችን፣ የቤተሰብ ኣባላትንም ጨምሮ ያስቀጣል። የሴቶች የግብረስጋ ብልት መግረዙ እዉጭ ኣገር እንኳን የተፈጸመ እንደሆን፣ ፈጻሚዉ ስዊዘርላንድ ዉስጥ ሊቀጣ ይችላል።
ከዚህም ኣልፎ፣ የሴቶች የግብረስጋ ብልት መግረዝ የዓለም ኣቀፍ ሕግን ስለሚጥስ፣ በብዙ ኣገሮች ዉስጥ የተከለከለ ነው።

## የሴቶችን የግብረስጋ ብልትን መግረዝ የሚከለክሉ ሕጎች



■ የተከለከለ ነው

የሴቶችን የግብረስጋ ብልትን መግረዝ የከለከሉ ኣገሮች: ሁሉም የምዕራብ ኤዉሮጳ ኣገሮች፣ ግብጽ፣ኢትዮጵያ፣ ኣዉስትራሊያ፣ ቤኒን፣ ቡርኪና ፋሶ፣ ኣይቬሪ ኮስት፣ ጂቡቲ፣ ኤርትራ፣ ጋና፣ ጊኒ፣ የመን፣ ካናዳ፣ ኬንያ፣ ማዉሪታንያ፣ ኒጀር፣ ናይጀሪያ፣ ኒውዚላንድ፣ ሴኔጋል፣ ሱዳን፣ ደቡብ ኣፍሪቃ፣ ታንዛኒያ፣ ቶጎ፣ ቻድ፣ ኡጋንዳ፣ ዩናይትድ ስቴትስ፣ የሴንትራል ኣፍሪቃ ሬፓብሊክ (2010 የወጣ ዘገባ)

በተለያዩ የኣፍሪቃ ኣገራት ዉስጥ በፊልምና በቴያትር መልክ እያዘጋጁ፣ ይሄንን ተግባር እንዳይፈጸም፣ መረጃ የመስጠት ቅስቀሳ በማድረግ፣ ግርዛትን የመከላከል ስራ በመስራት ላይ ይገኛሉ። ብዙዎች ሕብረተሰቦችም የሴቶች የግብረስጋ ብልት የመግረዝ ልማድ እንዳይቀጥል፣ በግልጽና በጋራ ሆነው ተቃዉሟቸዉን ገልጸዋል።

## ጠቃሚ የሆኑ ኣድራሻዎች

ለተጨማሪ ኣድራሻዎችና እርዳታ የሚያገኙበትን መንገዶች ለማወቅ ከፈለጉ የስዊዘርላንድን ካሪታስን ወይም የስዊዘርላንድ ቴረ ደ ፌም ጋር ይገናኙ።

**Caritas Schweiz – Vermittlungsstelle für die Prävention von Mädchenbeschneidung in der Schweiz,** Löwenstrasse 3, 6002 Luzern, 041 419 23 55 (የስዊዘርላንድ ካሪታስ፤ በስዊዘርላንድ የልጃገረዶች መገረዝን ለመከላከል ማገናኛ ማዕከል)

**TERRE DES FEMMES Schweiz,** Standstrasse 32, 3014 Bern, 031 311 38 79 (ቴረ ደ ፌም ስዊዘርላንድ)

### የሕክምና እርዳታዎች

**Frauenklinik Inselspital Bern,** Effingerstrasse 102, 3010 Bern, 031 632 16 14 (የሴቶች ክሊኒክ በርን)

**Centre hospitalier universitaire Vaudois, Département de Gynécologie et Obstétrique et de Génétique médicale** (በካንቶን ቫዶት የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል፤ የመውለድ፣ የጌንኖኮሎጊና የጄነቲክ ክፍል)

Unité psycho-sociale, Av. Pierre Decker, 1011 Lausanne, 021 314 32 45 (የሶሺያል ስነ ኣእምሮ ክፍል፣ ሉዛን)

Gynécologie pour adolescentes, UMSA, Av. Beaumont 48, 1011 Lausanne, 021 314 37 60 (የወጣቶች ጌንኖኮሎጊ፣ ሉዛን)

**Hôpitaux Universitaires de Genève (HUG)**

Département de gynécologie et obstétrique, 30, bd de la Cluse, 1205 Genève, 022 382 68 16 (የጌንኖኮሎጊና የወሊድ እርዳታ ክፍል)

Département de médecine communautaire et de premier recours, Planning Familial (CIFERN), 47, bd de la Cluse, 1205 Genève, 022 372 55 00 (የመከላከያና የመሰረታዊ ሕክምና ክፍል)

**Klinik für Gynäkologie, Universitätsspital Zürich,** Frauenklinikstrasse 10, 8091 Zürich, 044 255 50 36/37 (የጌኖኮሎጊ ክሊኒክ፣ የዩኒቨርስቲ ሆስፒታል ዙሪክ)

**Frauenklinik Universitätsspital Basel,** Spitalstrasse 21, 4031 Basel, 061 265 90 43 (የሴቶች ክሊኒክ የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል፣ ባዝል)

**Clinique Vert-Pré,** Centre de Chirurgie Plastique, 15 chemin de la Colombe, 1231 Conches / Genève, 022 704 31 13 (የፕላስቲክ ቀዶ ጥገና ማዕከል)

**Frauenklinik Kantonsspital St. Gallen,** Rorschacherstrasse 95, 9007 St. Gallen, 071 494 20 21 (የሴቶች ክሊኒክ የካንቶን ሆስፒታል፣ ሳንት ጋለን)

**Département gynécologie obstétrique CHCVS,** Hôpital de Sion, Avenue du Grand-Champsec 80, 1950 Sion, 027 603 42 16/17 (የጌንኖኮሎጊና የወሊድ እርዳታ ክፍል)

በኣካባቢዎ እርግዝናን እና የቤተሰብ ፕላንን በሚመለከት እርዳታ የሚያገኙበትን ኣድራሻ በሚቀጥለው ድረገጽ ያገኛሉ።
www.isis-info.ch

### ስደተኞች ሴቶች የሚገናኙበትና እርዳታ የሚያገኙበት ማዕከላት

**Bern:** Somalische Frauengruppe, 078 901 50 92 (በርን፡ የሶማሊያ ሴቶች ማሕበር)

**Genève:** Camarada (accueil et formation élémentaires pour femmes migrantes), Chemin de Villars 19, 1203 Genève, 022 344 03 39 (ለስደተኞ ሴቶች መሰረተ ትምህርትና እንክብካቤ፣ ጄነቭ)

**Lausanne:** Appartenances (accueil, orientation, espaces de rencontre, formation, soutien psychothérapeutique), Rue des Terreaux 10, 1000 Lausanne 9, 021 351 28 80 (እንክብካቤ፣ ምክር፣ መገናኛ ቦታ፣ ትምህርት፣ የስኖ ኣእምሮ ቴራፒ እርዳታ)

**Ostschweiz/Zürich:** Ostschweizerische Frauengruppe, 078 895 53 45 (ምስራቅ ስዊዘርላንድ/ ዙሪክ፡ የምስራቅ ስዊዘርላንድ ሴቶች ማሕበር)

**Sion:** Association KALKAL, 079 613 93 47 (የከልካር ኣሶሲየሽን፣ ጽዮን)

**Ticino:** Antenna MayDay, Via Merlina 3a/b, 6962 Viganello, 091 973 70 67 (ቴሲን) / Comunità africana del ticino, Lugano, 076 702 56 23 (የኣፍሪቃዊያን ኮምዩኒቲ በተሲን፣ ሉጋኖ)

### የጽሑፍ ምንጮች

© የፌደራል ጤና ጥበቃ መስሪያ ቤት (BAG)፣ የ BAG ማሰራጫ ቁጥር፡ GP 07.12 30EXT1205

ኣዘጋጅ፡
የፌደራል ጤና ጥበቃ መስሪያ ቤት፣ ኢ- ሜይል፡ migrationundgesundheit@bag.admin.ch, www.miges.admin.ch
ተረ ደ ፌም ስዊዘርላንድ፣ ኢ- ሜይል፡ info@terre-des-femmes.ch, www.terre-des-femmes.ch

ጽሑፍ፡ ተረ ደ ፌም ስዊዘርላንድ፣ ጽሑፉ የተዘጋጀው በኣማርኛ/Amharisch/Amharique ሐምሌ 2012፣ 2-ተኛ ዝግጅት፡ ይህ ጽሑፍ በጀርመንኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በዓረብኛ፣ በሶማልኛና በትግርኛ ቋንቋዎችም ተዘጋጅቷል።

ኣሰራጭ፡ www.migesplus.ch በብዙ ቋንቋዎች የቀረበ የጤንነት ኢንፎርሜሽን፣ የስዊዘርላንድ ቀይ መስቀል፣ የጤንነትና ኢንተግሬሽን ዲፓርትመንት ወይም www.terre-des-femmes.ch

ይሄ የኢንፎርሜሽን ጽሑፍ በሚገስፕሉስ ፋይናንሳዊና እውቀታዊ እርዳታ ተዘጋጅቶ የቀረበ፣ „ስደተኞችና ጤንነት 2008-2013“ በተባለው የብሔራዊ ፕሮግራም የተዘጋጀ ነው። ጽሑፉ የተዘጋጀው ከክሎሪን ነጻ ሆኖ በነጣ ወረቀት ነው።

Layout: www.alscher.ch

አማርኛ / Amharisch / Amharique



# የሴት ልጆች የብልት ግርዛት — ሴቶች ልጆቻችንን እንጠብቃለን

## ለወላጆችና ለተገረዙ ሴቶች መረጃ

Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra

Swiss Confederation

Federal Department of Home Affairs FDHA
**Federal Office of Public Health FOPH**

migesplus

TERRE DES FEMMES
Schweiz

የልጃገረዶችና የሴቶች መገረዝ ከባድ የጤና ችግር ያስከትላል። ስዊዘርላንድ ውስጥ የሴቶች ልጆች መገረዝ በሕግ የተከለከለ ነው።

## የሴቶች ብልት መገረዝ ምንድነው?

የሴቶችን የግብረስጋ ብልት መግረዝ፣ የሕክምና ምክንያት የሌለው ሲሆን፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የውጭዉን የብልት ኣካላቸዉን ቆርጦ ማስወገድ ወይም ተጨማሪ የኣካል ጉዳት ማድረስ ነው። የሴቶች የግብረስጋ ብልት መገረዝ የብልታቸዉን የላይኛዉን ከንፈር ከነቂንጢሩ ወይም ቂንጢሩን ትንሽ ትቶ ማስወገድን (ኢንሴሽን/ ሱና)፣ ቂንጢሩንና የዉስጠኛው ከንፈሩን ቆርጦ ማስወገድ (ኤክሴሽን) እና ትልቁን ከንፈሩን ትንሽ ቀዳዳ ብቻ ትቶ እንደገና መስፋትን (ኢንፋቢሌሽንን) ያጠቃልላል።

የሴቶች የግብረስጋ ብልት መገረዝ ሌሎቹንም የሴቶችን የግብረስጋ ብልት ላይ ጉዳት የሚያደርሱትንም ልማዶችንም ይጨምራል። (ለምሳሌ፡ ቂንጢራቸዉን መዉጋት፣ መቁረጥ፣ መጫርና ማቃጠልንም ያጠቃልላል።)

## የሴቶች የግብረስጋ ብልት መግረዝ ምን ዓይነት የጤና ችግር ሊያስከትል ይችላል?

የሴቶች የግብረስጋ ብልት መግረዝ

ከባድ የደም መፍሰስ

በመገረዝ ምክንያት የሚፈጠረው የጠባሳው ዉስብስብነት (የመግልና የዕብጠት መፈጠር)

ኢንፌክሺን (የደም መመረዝ፣ ቲታኑስ ወ.ዘ.ተ.)

የግብረስጋ ብልቱ ኣከባቢና በታችኛው የሆዳቸው ኣከባቢ ላይ በሚደርሰው መመርቀዝ ምክንያት የሚ ከተለው መሃንነት

ከተፈጥሮ ዉጭ ለሆነ ረጂም ምጥንና እናትና የሚወለደዉን ልጅንም ጭምር ከፍ ባለ ሁኔ ታ ለሞት መዳረግን

የኣእምሮ ስቃይን
ወዲያው የሚደርሱ ችግሮች፥ ከባድ ፍርሃት፣ ድንጋጤ፣ ቅጀት
ለረጅም ዘመን የሚደርሱ ችግሮች፥ የኣእምሮ ጭንቀት፣ የእንቅልፍ ማጣት፣ በቀላሉ መደንገጥ፣ የማስታወስ ችሎታ ማጣት

ሞት

ከባድ ስቃይ

በወር ኣበባ ጊዜና ሽንት ሲሸኑ የሚያጋጥማቸው ስቃይና፣ እንዲሁም ሽንታቸዉን መቋጠር ኣለመቻል

ዝቅ ያለ የግብረስጋ ግንኙነት ስሜትና ሕመም፣ ሴቷን የግብረስጋ ግንኙነትን እንዳትረካበት ያደርጋታል። በዚህም ምክንያት ወንዱ የግብረስጋ ግንኙነት እርካታዉን ስለማያገኝ፣ ባጠቃላይ በባልና በሚስት መካከል ሊኖር የሚገባዉን ግኑኙነትንም ጭምር ሊያበላሽና ሊበክል ይችላል።

እንደ ኣገራረዙ ዓይነትና ሁኔታ፣ በጤንነት ላይ የሚደርሰው ዉስብስብነትም የተለያየ ነው።

## ለተገረዙ ሴቶች የተሰጠ መረጃ

ግርዛትን ወደ ኋላ መመለስ ኣይቻልም። በመገረዝ ምክንያት ለተፈጠሩት ዉስብስቦች ግን የሕክምና እርዳታ ሊደረግላቸው ይችላል። ከዚህም ኣልፎ በቀዶ ጥገናዊ መንገድ፣ የብልትን ቀዳዳ ማስፋትና ቂንጥርንም በከፊልም ቢሆን መልሶ ለመጠገን  ይቻላል።

### የርስዎ መብት

በጉዳይዎ ኣስፈላጊ መረጃ የማግኘትና የሕክምና ባለሙያዎች የሚሰጡትን ማብራርያዎች የመረዳት መብት ኣለዎት። የቋንቋ ችግር ያለዎት ከሆነ፣ ኣስተርጓሚት እንድትመጣልዎ መጠየቅ ይችላሉ።

እርስዎ ከሚያምኑት ባለሙያ ጋር በጉዳይዎ ይነጋገሩ።

ከሕክምና ባለሙያ ጋር ሳያቅማሙ በግልጽ ይነጋገሩ። ባለሙያዎቹ መገረዝን በሚመለከት ሁሉ ጊዜ የተሻለ እዉቀት ስላላቸው፣ ኣርስዎን በሚገባ የሕክምና እርዳታ እንዲያገኙ የተቻላቸዉን ያህል ይጥራሉ።

### እርግዝናና መዉለድ

በርግዝና ወቅት፣ በተለይ ከመገረዝዎ ጋር በተያያዘው ምክንያት፣ ለመዉለዱ የሚደረጉትን ዝግጅቶችን ለመመካከር፣ በተቻለዎት መጠን በጊዜው ከሓኪሞችዎ ጋር ይነጋገሩ።

### የስነ ኣእምሮ እርዳታዎች

ኣስፈላጊ መስሎ ከታየዎት የስነ ኣእምሮኣዊ ረዳትንና ሽኚን ለማግኘት ይጠይቁ።

የሴት የግብረስጋ ብልት የተሰፋ ከሆነ (ኢንፋቢሌሽን)፣ በቀዶ ጥገና ስፌቱን በመፍታት (ዲፋቢሌሽን) ሊከተሉ የሚችሉ የጤና ሰበቦችን መቀነስ ይቻላል። በቀዶ ጥገናው ብልቱን የዘጋው ጠባሳ ይከፈታል። የዚህ ዓይነት ቀዶ ጥገና በከፊል፤ በወር ኣበባ ወቅት ኣብዛኛው ጊዜ የሚከሰተውን ስቃይ፣ ሽንት ለመሽናት የሚከሰተውን ችግር፣ ኣብዛኛው ጊዜ የሚከሰተውን የፍኛ መመርቀዝ፣ ከመጀመሪያው በፊት ወይም ስቃይ ካለው የግብረስጋ ግኑኝነትና በመውለድ ጊዜ ያሉትን ስቃዮችንና የጤና ችግሮችን ይቀንሳል።በዚህም ምክንያት ተሰፍተው የነበሩ ሴቶች በቀዶ ጥገና ልጅ የመውለድ ግዴታ ኣይኖባቸውም። ተሰፍቶ የነበረዉን ጠባሳ በመፍታት ወይም በዲፋሌሽን፣ ተፈጥሮኣዊ በሆነ መንገድ ልጅ መውለድ ይቻላል። ዲፋቢሌሽኑ ከመውለድ በፊትም ሆነ በመውለድ ጊዜም ሊደረግ ይቻላል። ሕጻኑ ከተወለደ በኋላ ኢንፋቢሌሽን ወይም መልሶ የግብረ ስጋ መሰፋት ኣይደረግም።

## ሌሎች ሰዎች የሴቶችን የግብረስጋ ብልት ግርዛትን በተመለከተ ምን ኣስተያየት ይሰጣሉ?

„ማንም ሰው ሃይማኖትህ ስህተት ነው ኣይልህም፣ ማንም ሰው ያንተን ባህልና ልማድን ስህተት ነው ኣይልህም። እኛ በቀላሉ የምንለው ነገር ቢኖር፣ የሴቶች የግብረስጋ ብልት መግረዝ ልክ ኣይደለም ነው። ኣሁን በ21ኛ ክፍለ ዘመን ስለምንገኝ፣ የሴቶችን ግርዛት ታሪክ እናድርገው።“

ማርክ ኢማኑኤል፣ የኣፍሪቃ ማይረር ፋዉንዴሽን

„እግዚኣብሔር ኣንተን የተሟላ ፍጡር ኣድርጎ ነው የፈጠረህ። ቂንጢር መፈጠር ኣልነበረበትም የሚሉ ሰዎች፣ የእግዚኣብሔርን የመፍጠር እዉቀቱን የሚጠራጠሩ ወይም የጥያቄ ምልክት ዉስጥ የሚያስገቡ ሰዎች ናቸዉን?“

ሼክ ኣብዱላሂ ጉዶው፥ የሃይማኖት ምሑር

„እኛ ጥሩ ባህል ኣለን ብለን እንናገራለን። ልጆቻችንን እንወዳለን። የሕብረተሰባችን ኣባላት የሆኑትን ኣረጋዊያኖችን እናከብራለን፣ እያረጁ ሲሄዱም እንንከባከባቸዋለን። እነዚህ ባህርያት ቀጣይነት እንዲኖራቸው ኣሁንም እንፈልጋለን። ሴቶቻችንንና ልጃገሮዳችንን የሚያጠቁ ልማዶች ግን መቀየር ኣለባቸው።“

ዘይነብ ኣሕመድ፥ ዩኒሴፍ ኬኒያ

„ባህላት ቆመው የሚቀሩ ነገሮች ኣይደሉም። ተለዋዋጭ ናቸው። ኣዲስ የሆኑ ሚዛኖች ይፈጠራሉ፣ ኣዲስ የሆኑ መረጃዎችም ይቀሰማሉ። ይሄ የማይቀርለት የሕብረተሰቦች የለውጥ ጉዞም የሴቶችን የግብረስጋ ብልት ግርዛትን የጥያቄ ምልክት ዉስጥ ያስገባል።“

ብርሃነ ራስወርቅ፥ የኢንተር ኣፍሪቃ ኮሚቴ ፕሬሲደንት

„ያልተገረዘች ሚስት ማግባት የሚፈልጉ ወንዶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣት ላይ ነው ያለው። ምክንያቱም፡ ኣንደኛው ሴትዮዋ የመሰቃየት ስሜት ስለማይኖራትና የበለጠም ስሜት ስለሚኖራት፣ ሁለተኛው ደግሞ ወንዱ ራሱን የመውቀስና የይሉኝታ ስሜትም ስለማይኖረዉ ነው።“

ጀማል መሓመድ

„ሴት ልጅን የመግረዝ ልማድ፣ ሴቷን በልጃገረድነቷ እንድትቆይም ይሁን ወይም የኣመንዝራነት ጸባያት እንዳይኖራት የመከላከያ ዋስትናን ኣይሰጥም። ወላድ እንድትሆንም ዋስትናን ኣይሰጥም። በተቃራኒዉ ግን መግረዝ ኣብዛኛው ጊዜ ሴቷን ለኣካሏ መመርቀዝ ያጋልጣታል። በዚህም ምክንያት መሃን የመሆን ዕድሏ ከፍ ሊል ይችላል።“

ብርሃነ ራስወርቅ፥ የኢንተር ኣፍሪቃ ኮሚቴ ፕሬሲደንት